## **የአቶ ሲሳይ መንግስቱ አዲሱ የመልስ መልስ፤ የ"ካፈርኩ አይመልሰኝ!" ክርክር ተጨባጭ ማሳያ**

**መታሰቢያ መ.**

**መስከረም 28፣ 2010 ዓ.ም.**

በመጀመሪያ በመረጡት ርእሰ-ጉዳይ ዙሪያ የመሰላቸውን ሀሳብ በፅሑፍ አቅርበው እንድንወያይ እድል ስለ ሰጡን አቶ ሲሳይ መንግስቴ አዲሱን ላመሰግናቸው እወዳለሁ። ሁላችንም በአገራችን መልካም የተባለ ነገር ሁሉ ሰፍኖ፤ በተቻለ መጠን ችግሮችን ተወግደው ማየት እንደምንሻም ፅኑ እምነቴ ነው። ምንም እንኳን የፍላጎት ልዩነት ላይኖረን ቢችልም የምንመርጠው መንገድ ግን እንደየ ግንዛቤያችን ሊለያይ እንደሚችልም እረዳለሁ። ስህተት የመሰለን ነገር ሲኖር በሰለጠነ መንገድ አንዳችን ሌላችንን ለማረም ሀሳብ ብናቀርብም ቀና አካሄድ ነው። እንዲህ ሲሆን የኔ ሀሳብ ለምን ይተቻል ብለን ካሰብን ወይም ሀሳባችንን ስህተት መሆኑ ሲነገረን ክብራችን የተነካ ከመሰለን እና አጉራ ዘለል የሆነ መልስ ለመስጠት ከተነሳሳን ግን ነገር ተበላሸ ማለት ነው። እውነት ለመናገር የአሁኑ የአቶ ሲሳይ ፅሁፍ መልስ ለመስጠት ይመጥናል የሚል እምነት የለኝም ነገር ግን አንዳንድ ወገኖቻችን የሌላኛውን ዝምታ ወደ ከፋ ስህተት እንዲያመሩ እያደፋፈራቸው እንደሆነ ስመለከት መልስ ለመፃፍ ወሰኛለሁ። አሁን በያዙት የ"ካፈርኩ አይመልሰኝ" መንገድ ክርክሩን ለመቀጠል ከመረጡም እኔም መልስ መስጠቴን እንደምቀጥል ለአቶ ሲሳይ ላረጋግጥላቸው እወዳለሁ።

አቶ ሲሳይ በእኔ እንዲሁም በቀለሙ በለጠ የመልስ ፅሁፎች ላይ መልስ ብለው ያስነበቡንን ፅሁፍ "ከሁሉም የከፋው ውድቀት ስህተትን ለማረም ዝግጁ አለመሆን ነው!!" የሚል ርእስ ሰጥተውታል። ስህተትን ለማረም ዝግጁ አለመሆን የውድቀት መንገድ እንደሆነ ሳይታለም የተፈታ ነው፤ ስለዚህ በዚህ ሀሳብ ላይ ከአቶ ሲሳይ ጋር እስማማለሁ። መመለስ ያለበት ጥያቄ ግን "ታዲያ ማን ነው በዚህ መንገድ ውስጥ የሰመጠው?" የሚለውን ነው። ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ወደ ክርክሮቹ መለስ ብለን ዝርዝሮቹን ማየት ያስፈልገናል።

ለመጀመር ያህል፤ በብአዴን ዙሪያ በተፃፈው የአቶ ሲሳይ ፅሁፍ የተነሱትን አንዳንድ ጉዳዮች ቢታዩ እንደምስማማ፤ በአንዳንዶቹ በተለይ ከይዘት ጋር የተያያዙትን ጉዳዮች ላይ የተሰጠውን መደምደሚያ ግን ችኩል እና በቂ ማስረጃ ያልቀረበበት እንደሆነ መግለፄ አቶ ሲሳይ አምርረው ጠልተውታል። ከአስተሳሰብ አኳያ የምንስማማበትን ጉዳይ እንደምንስማማበት፤ የተሳሳተ የመሰለንን ጉዳይ ደግሞ በምክንያት በማስደገፍ መቃወም ትክክለኛ መንገድ አይደለም እንዴ? ጭራሽ የdouble standard ማሳያ እንደሆነ ለመግለፅም ሞክሯል። በነገራችን ላይ ብአዴን በይዘቱ ሁሉንም የአማራ ክልል ህዝቦች በእኩልነት እና በተመጣጣኝነት እንደሚወክል እና ሁሉንም እንዲያልፍላቸው እየተጋ እንደሆነ ጥርጥር የለኝም። ቀለሙ በለጠም በብዙ ማሳያዎች ለአቶ ሲሳይ በሰጡት መልስ አብራርተውላቸዋል። በእርግጥ በየትኛውም የአገራችን ገዢ ፓርቲ እና ክልል እንደሚታየው ሁሉ በብአዴን ወይም በአማራ ክልልም የተለያዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዳሉ ግልፅ ነው።

ታዲያ አቶ ሲሳይ ይዘት ላይ የሰጡትን በማስረጃ ያልተደገፈ እና የተሳሳተ መደምደሚያ ስህተት እንደሆነ ስንገልፅላቸው ማሳያ ጠቅሰው እንደመከራከር ለምን እኔ ባነሳሁት የብአዴን የስያሜ ሀሳብ ላይ ተስማምተህ ስታበቃ ይዘቱ ላይ ግን ትቃወማለህ ወይም ታዲያ ለምን በህወሓት ላይ ሲሆን በሁለቱም (በስያሜም በይዘትም) ተቃወምክ የሚል ጉንጭ አልፋ (የራሳቸውን አባባል ልዋስና) ክርክር ያነሳሉ። ይሄንን ክርክራቸው ሳነብ እንዲያውም መልስ

ባልሰጥበትስ፤ ለዚህ መልስ መስጠት ይገባልን? የሚል ሀሳብ እየተፈታተኝ ነበር። ግድ የለም ልቀጥል... እኔ ያነሳሁት ክርክር እኮ ግልፅ ነው። በብአዴን ስያሜ ዙሪያ ያነሱትን ሀሳብ ብአዴን አይቶ ቢያስተካክለው ጠቃሚ ይሆን እንደሆነ እንጂ ምንም ጉዳት እንደማይኖረው፤ እንዲያውም በተጨባጭ በብአዴን ውስጥ ያለውን ይዘት እንደሚያንፀባርቅ መስማማቴ አቶ ሲሳይን ለምን እንዳስቆጫቸው ከቶ ሊገባኝ አልቻለም። የኔ ምክንያት ግልፅ ነው። ብአዴን "ብሄረ አማራ" ስለሚል እና ሌሎቹ በክልሉ ያሉ ብሄር/ብሄረሰቦች/ህዝቦች በተጨባጭ የእነሱም ጭምር የሆነውን ገዢ ፓርቲ ስያሜው ብዝሀነትን የሚያንፀባርቅ እንዲሆን ሊፈልጉ ስለሚችሉ ነው (ምንም እንኳን ዋናው ቁም ነገሩ ይዘት እና ተግባር ቢሆንም)። በህወሓት ላይ ያነሱትን የስያሜም የይዘትም ትችትዎ ግን ግልፅ ስህተት ነው እኮ ነው የምልዎት።

እስኪ በሚከተሉት ጥያቄዎች እና ጉዳዮች ዙሪያ ያለዎትን መልስ እና ሀሳብ በቀናነት እና በቀጥታ ይንገሩን፤

1. ለምን በዜጎች መፈናቀል ችግር ላይ ብቻ ተንተርሰው ብአዴን አማራን አይወክልም የሚል ድምዳሜ ላይ ደረሱ፤ ያስኬዳል ወይ? ለምን ብአዴን ሁሉንም የአማራ ክልል ህዝቦች ተጠቃሚ ለማድረግ የሚለፋ እንደሆነ፤ የክልሉን የውስጥ ብዝሀነት በሚገባ እንደሚያስተናግድ የተነሳውን የቀለሙ በለጠ ሀሳብ በተጨባጭ ማስረጃ አይሞግቱም፤ ዳር ዳሩን ከመርገጥ ይልቅ።

2. ለምን የመፈናቀል ድርጊት በትግራይ ተወላጆች ላይ ተፈፅሞ እያለ ልክ ብአዴን ላይ እንዳደረጉት ይሄንን ማሳያ በመጥቀስ ህወሓት ትግርኛ ተናጋሪዎችን ወይም ትግራዮችን አይወክልም አላሉም (እንዲህ ቢሉም ዞሮ ዞሮ ስህተት ቢሆንም)?

3. ለምን የውሸት የአማርኛ ትርጉም በህወሓት ስያሜ ላይ እንደሰጡ የሚያትተውን ትችት መልስ አልሰጡበትም ወይም አይታረሙበትን፤ ስህተትን ለማረም አለመዘጋጀት እርስዎ እንደገለፁት የውድቀት መንገድ ስለ ሆነ።

4. "ለምሳሌ በቆቦና ሰሜን ጎንደር ዞኖችስ ነባር የትግራይ ተወላጆች የሉም?" የሚለውን ጥያቄ ለምን መልስ አልሰጡበትም? ምነው በትግራይ ላይ የሚያነሱትን ትችት (ትክክል ባይሆንም) በሌሎቹ ክልሎች ማንሳት ዳገት ሆነብዎት? ስለ ትግራይ የሚያነሱዋቸውን ትችቶች ምን ያህል ቀና ናቸው? ለትግራይ ሲሆን በዛ ክልል ላለው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የተለየ ምክርቤት ወይ ውክልና እንዲመቻችለት ጠይቀው ሲያበቁ በሌሎቹ ክልሎች (አማራን ጨምሮ) ዝምታን መምረጥዎ ትንሽ አያሳፍርዎትም? ለሁሉም በየትኛውም ክልል የሚኖር ብሄር/ብሄረሰብ የተለየ ምክርቤት ይኑረው ወይም የተለየ የውክልና መንገድ ይበጅለት ከተባለ እኮ ሁሉንም ክልሎች የሚመለከት እንጂ የትግራይ ጉዳይ ብቻ አይደለም ተብሎ እንዲነገርዎት ነው የሚፈልጉት ወይስ ማንም መልስ ሳይሰጥበት ታልፎ የትግራይ አጀንዳ ብቻ ሆኖ ማየት ነው ምኞትዎ? አመልካች ጣትዎን ሌላኛው ወገን ላይ ሲቀስሩ ሌሎቹ ሶስት ጣቶችዎ መልሰው ወደ እርስዎ እንደሚያመለክቱ ባይዘነጉትስ? ደግነቱ አሁን አሁን ጣት መቀሳሰሩ የጥፋት መንገድ እንደሆነ ለማንም ግልፅ ሆኖዋል። ስለዚህ ሰሚ አይኖርዎትም።

5. የቱ ላይ ነው እኔ በብአዴን አደረጃጀት ዙሪያ አስተያየት የሰጠሁት ወይም ከእርስዎ ሀሳብ ጋር የተስማማሁት? በስያሜ ላይ የተነሳውን ሀሳብ ቢታይ መልካም ነው ማለት ለእርስዎ በብአዴን አደረጃጀትም ጭምር ስለ ተሰጠው

አስተያየት መስማማቴን ያሳያል ማለት ነው? ስያሜ እና አደረጃጀት ምን አገናኝቶት? አሁንም ስህተትዎን እንዲያርሙ ዕድሉን ልስጥዎት!

6. የትግራይ ወጣት ምሁራን ብሄራችን "ትግሬ" አይደለም ብለው ነበር ወዘተ. እያሉ መቀባጠር ለምን አስፈለግዎት? ማንስ "ትግሬ" ነው የሚባለው አለ? "ትግራይ" የትግርኛ ተናጋሪዎች የብሄር ስያሜ እና የክልሉ ስያሜ ሊሆን አይችልም እንዴ? የትግራይ ህገ መንግስት በ**ትግራይ ክልል** ትግራይ፣ ኢሮብ እና ኩናማ የሚባሉ መኖራቸውን መግለፁ እና የድርጅቱ ስያሜ ደግሞ "ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ" እንጂ አቶ ሲሳይ በቅጥፈት እንዳስቀመጡት "የትግራይ **ህዝብ** አብዮታዊ ነጻ አውጭ ግንባር (ትህአነግ)" የማይል መሆኑስ የእኔን ሀሳብ ነው የሚያጠናክረው ወይስ የእርስዎን "የካፈርኩ አይመልሰኝ" ክርክር። "የትግራይ ህዝብ" ቢልም "የትግራይ ብሄር" እስካላለ ድረስ ሊያከራክር እንደሚችል እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነው። እኔ የፃፍኩት እኮ ህወሓት የሚለውን ስያሜ የትግርኛ ተናጋሪውን ህዝብ ስም ብቻ እንደሚያንፀባርቅ አድርገው ያስቀመጡትን የውሸት ትርጉም እንደሆነ እና ሊታረሙ እንደሚገባ የሚገልፅ ሀሳብ ነው። አሁንም የውድቀት መንገዱን ከመረጡ አለመታረም የእርስዎ ምርጫ ነው።

7. ለምን በ1968ቱ ማኒፌስቶም ጭምር በግልፅ የተቀመጠውን ትግራይ እነማን እንደሚያካትት እንዲመለከቱ የተነገርዎትን ሀሳብ መልስ አይሰጡበትም? በሀሳብ ሙግት የሚያምኑ ከሆነ ማለቴ ነው፤ ወይስ ውሀ አያነሳም፣ ጉንጭ አልፋ ነው፣ ወዘተ. ስላሉ ብቻ የሚያሳምኑን መሰልዎታል?

8. በሌላ በኩል ደግሞ ህወሓት ትግርኛ ተናጋውን አይወክልም የሚል ሀሳብ የተነሳ ይመስል ክርክሩ ወደ ሌላ ሲወስዱት ይታያል፤ እንዲህ በማለት "በአጠቃላይ ህወሓት የትግራይ ብሄር ህዝብ ወኪል መሆኑን በበርካታ ማስረጃዎች ማረጋገጥ ቢቻልም በአሁኑ ወቅት ይህ አስመልክቶ ጉንጭ አልፋ የሆነ ክርክር ውስጥ መግባት ያለብን አይመስለኝም"። ህወሓት የትግርኛ ተናጋሪው ህዝብ ወኪል አይደለም የሚል ሀሳብ ያነሳ ሰው አለ እንዴ? የተነሳው ሀሳብ እኮ ህወሓት የሚወክለው ትግርኛ ተናጋሪውን ብቻ ሳይሆን ሌሎች የትግራይ ህዝቦችም ጭምር ነው የሚል ነው። የአቶ ሲሳይ ተረት የኩናማ እና የኢሮብ ህዝቦች እንዲሁም ሌሎች እና ከነዚህ ህዝቦች አብራክ የወጡ የህወሓት ታጋዮች አይስሙት ያስብላል!

9. የቱ ጋር ነው የተውገረገረ፣ ምክንያት ላይ ያልተመሰረተ፣ በእርስዎ ስብእና ላይ የተመሰረተ ወይም ፀሀይ የሞቀውን እውነት የካደ ክርክር ያቀረብኩት? ፅሁፍዎ እነዚህን ቃላት እና ሀረጎች በመደርደር ከመጀመር ይልቅ ቁም ነገሩ ላይ ቢያተኩሩ አይሻልም ነበር? ወይስ እንደዛ ብለው ስለ ተናገሩ ብቻ መልስ እንደሰጡ ይቆጠራል?

10. አቶ ሲሳይ እንዳነብም መከረውኛል። ለዛም እጅግ ግልፅ በሆነው በህወሓት ስያሜ ዙሪያ። ስለ ምክርዎት አመሰግናለሁ! በምክርዎት ዙሪያ ሰፊ መልስ መስጠት እችል ነበር ነገር ግን ለሌሎቹ አንባቢዎች ክብር ስል እቆጠባለሁ። የተወሰኑ ጥያቄዎች ብቻ ልጠይቅዎት፤ ክርክሮች ወደ ግለሰቦች ስብእና መውረድ እንደሌለባቸው "እንደመከሩን" ከመቸው ረሱት? ለመሆኑ ሌሎች እንዲያነቡ ምክር እንዲሰጡ ያደፋፈርዎት ምንድን ነው? ከአንባቢነትዎ ብዛት የተነሳ "ማትሪክን በጥሰው" ወደ የትኛው ዩኒቨርስቲ ነበር የገቡት እባክዎት? እድሜ እዚህ ላደረስዎት ብአዴን (ውለታውን ዘንግተው ሊያጨቀዩት ሌት ተቀን ቢተጉም) ስለ ንባብ እና እውቀት መካሪ ለመሆን እየቃጣዎት ነው....

እውነትም "ከሁሉም የከፋው ውድቀት ስህተትን ለማረም ዝግጁ አለመሆን ነው!!"

**ቸር ይግጠመን!**